# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

## የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2012

ህዳር /2012 ዓ/ም

ባህር ዳር

# የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2012

1. **አውጪው ባለስልጣን**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ክልል መስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 163/2010 አንቀጽ 22 ንኡስ አንቀጽ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

2. **አጭር ርዕስ፤**

ይህ መመሪያ **"የታክስ ወኪልነት ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 6/2012"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ፤**

በአዋጁ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ በአዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ከዚህ በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል፡-

1) **"የታክስ ወኪል"** ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 95 መሠረት ፈቃድ የተሠጠው የታክስ ወኪል ነው፡፡
2) **"የታክስ ወኪልነት አገልግሎት"** ማለት በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 94 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ታክስ ከፋዮች ከገቢዎች ቢሮ ጋር ለሚኖራቸው ጉዳዮች ታክስ ከፋዮችን በመወከል ከገቢዎች ቢሮ ጋር ማንኛውንም አይነት የሥራ ግንኙነት ማድረግ ነው።
3) **"የታክስ ወኪልነት የሙያ ፈቃድ"** ማለት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት ብቃት ያለው ስለመሆኑ በገቢዎች ቢሮ የሚሰጥ የሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ነው፡፡
4) **"የታክስ ወኪልነት ንግድ ስራ ፈቃድ"** ማለት የታክስ ወኪልነት አገልግሎት ለመስጠት በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ መሰረት አግባብ ባለው ፈቃድ ሰጪ አካል የሚሰጥ የንግድ ስራ ፈቃድ ነው፡፡
5) **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት ታክስ ወኪሉ ሊያስወግዳቸው የማይችሉ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች በተወሰነ አካባቢ የተነሳ ወይም የተፈጠረ ጦርነት ፣ቃጠሎ፣የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ጽኑ ህመም ሲኖር እና ይህም በታክስ ወኪሉ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ ሲኖረው ነው፡፡
6) **"አዋጅ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው፡፡